# የመላ ኢትዮጵያ ሶሺሊስት ንቅናቄ
# (መኢሶን)

# ፕሮግራም

ሚያዝያ 2005

# መቅድም

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ከተመሰረተበት ዘመን ጀምሮ፤ የኢትዮጵያን ሁኔታ፣ የአለም አቀፉን ሁኔታ እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚከሰቱ የአስተሳሰብ ለውጦችን አመላክቶ፤ በፕሮግራሙ ላይ አስፈላጊ ማሻሻዮችን እያካተተና ለወቅታዊ ትግል ምቹ ሁኔታዎችን እያስተካከለ ሲታገል የቆየ አንጋፋ የፖለቲካ ድርጅት ነው።

ምንም እንኳን መኢሶን ዛሬ በሐገራችን ለሚታየው የሰብዓዊ መብት፣ የፖለቲካና የሃይማኖት ነጻነት፣ ለፍትህና ለህዝቦች እኩልነት ለሚደረገው ትግል በር ከፋች ድርጅት ቀዳሚው ቢሆንም፤ ባለፉት አስርተ አመታት ስለጋራ ትግል እንጂ ስለራሱ ምንም ዓይነት ማስተዋወቅ ባለማድረጉ አብ ዛኛው ወጣት ትውልድ በጥሞና አያውቀውም፤ ጥቂቶች የሚያውቁት ቢኖሩም ባሉባልታና በተጋነኑ አሉታዊ ድርጊቶች ነው።

ስለሆነም፤ መኢሶን ምን አይነት ድርጅት እንደሆነ ወደሚያብራሩ ጽሁፎች የሚያመለክት አጭር ገለጣ በዚህ መቅድም አማካይነት፣ ለፕሮገራሙ ተመልካቾች ያቀርባል። ይህ አጭር ማብራሪያ፣ ታሪክ ነክ እንደመሆኑ መጠን አንድ አንድ የሚጠቀሱ ተግባራት፣ ታሪኩ በሚነገርበት ዘመን የነበሩ ድርጅቶችን ሊመለከት ይችላል። ይሁንና በስም ከሚጠቀሱት እንደ ደርግና ወያኔ ካሉት፣ የወጣላቸው ጸረ ሕዝብ ድርጅቶች በስተቀር መኢሶን ባለፈ ታሪክ አሳቦ፣ ማንኛውንም ድርጅት የማይከስና በማንም ላይ ቂም እንደሌለው ያረጋግጣል።

መኢሶን ከስመ ጥሩው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አብራክ፣ በሃምሌ ወር 1960 ዓ ም፣ በሃምበርግ ከተማ (ጀርመን) በተደረገ ጉባኤ በህቡእ ተመሰረተ። ድርጅቱ በተመሰረተበት ወቅት ኢትዮጵያ አገራችን በፊውዳል አገዛዝ ጨለማ ውስጥ የምትዳክር አገር ነበረች። በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአገሪቱ ላይ የሰፈነው የከፊል ፊውዳልና ከፊል ካፒታሊስት ሥርዓተ ማህበር የኢትዮጵያን አምራች ሕዝብ ለከፍተኛ ብዝበዛና ጭቆና፣ ድህነት፣ ድንቁርናና ችጋር ያጋለጠ ሥርዓት ነበር። ሥርዓቱ የንጉሠ ነገሥቱን ፈላጭ ቆራጪነት አግንኖ ያሰፈነ፣ የጥቂት መሳፍንት፣ መኳንንትና የከፍተኛ ባለስ ልጣኖችን ጥቅም የሚንከባከብ ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ነበር። በተለይም ከሕዝቡ 90% በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ አምራች ገበሬ በሚመለከተው ከመሬት ጥያቄ አንጻር አንዳችም ለውጥ ለማድረግ የማይፈልግ ወይም የማይችል፣ የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች ለመመለስ የተሳነው፣ የብሄሮችን መብት ረግጦ የሚገዛ፣ በስልጣን መባለግን፣ በዘመድ አዝማድና በአምቻ ጋብቻ መጠ ቃቀምን አስፋፍቶ ያሰፈነ አገዛዝ ነበር። የነዚህ ሁኔታዎች ድምር በንጉሠ ነገ ሥቱ ዘመን፣ በየመልኩ ለመሬት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰብዓዊ መብቶች፣ ለፍትሃዊ አስተዳደርና ለዳኝነት፣ ለብሄሮች መብቶች መታወቅና መከበር፣ ወዘተ ትግል በመቀስቀሱ፤ በፊውዳሉ ዘመን በተለይ ከ50ዎቹ ዓመታት ወዲህ ባለው ጊዜ

ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነባትና የተረጋጋች አገር አልነበረችም። በተጠቀሱት ወሳኝና ሕዝባዊ ጥያቄዎች ዙሪያ በሚካሄደው ትግል በተለይ የየካቲትን አብዮት በቀደሙት አስር አመታት "ዴሞክራሲ፣ መሬት ላራሹና የብሄሮች መብት" በሚሉ ቁልፍ እሴቶች ዙሪያ የተማሪው ንቅናቄ እየተስፋፋና እየዳበረ ሲመጣ የድርጅታችን መስራቾች የነዚህ እንቅስቃሴዎች አካልና ግንባር ቀደም መሪዎች ስለነበሩ ለቀጣዩ ትግል ለመዘጋጀት መኢሶንን መሰረቱ።

በወቅቱ ድርጅታችን የማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ርዕዮተ ዓለም በመቀበል የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮትን መስመር ቀይሶ ሶሻሊስት ሥርዓት ማስፈንን ግቡ አድርጎ፤ እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በተለይ በኢትዮጵያ ዴሞክራቶች፣ አገር ወዳድ ሃይሎች፣ በምሁራንና በተማሪዎች ዙሪያ፤ የየካቲት አብዮትን ፍንዳታ በቀደሙት አመታት፣ በአገር ውስጥም፤ በውጭ አገርም፣ ይፋ ባልሆነ መንገድ ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ የምሁራን ድርጅት ነበር። ዋና አላማው ብሎ የተነሳበት አጀንዳም የፊውዳሊዝምን፣ የቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን ቀንበር አስወግዶ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፍትህ የሰፈነባት፣ ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩባት አንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የመመስረት አላማ ነበር።

የየካቲት አብዮት ፈንድቶ፤ በዚያ ስፋቱ፣ በዚያ ሃይሉና በዚያ ፍጥነቱ ሲገሰግስ መኢሶን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ይቋቋም፣ ሕዝባዊ ኮሚቴዎች ያብቡ፣ የተራማጆች ህብረት ይመስረት፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይለቀቁ፣ መሬት ላራሹ ይሁን፣ ፈላጭ ቆራጭ የዘውድ አገዛዝ ያክትም፣ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም...የሚሉትን አደራጅና አራማጅ ጥሪዎች በጽሁፍና በተለያዩ መንገዶች እያስተላለፈ የሕዝቡን ትግል ለማበረታታትና ፈር ለማስያዝ ከፍተኛ ጥረት አደረገ። የሕዝቡ ተጋድሎ

የተጠበቀውን ፍሬ ሰጥቶ በተለይም የካቲት 25. 1967 ዓ. ም የፊውዳሉን ሥርዓት የደመሰሰው የመሬት ላራሹ አዋጅ ሲወጣ፤ የፊውዳሉ ሥርዓት ደጋፊዎች፣ በባዕዳን የኢትዮጵያና በአብዮታችን ጠላቶች ድጋፍ፣ ይህንን ስር ነቀል አዋጅ በትጥቅ ትግል ጭምር ለመቀልበስ ሲንቀሳቀሱ፤ ድርጅቱ ቀደም ሲል በደርጉ ላይ የነበረውን የፍፁም ተቃውሞ አቋምና የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት ጥያቄውን አንስቶ "ሂሳዊ ድጋፍ" በሚል መስመር ተሰማራ።

ይህ መስመር፣ መኢሶን የወቅቱን ቅራኔዎች አቀማመጥና የመደቦች አሰላለፍ ያጤነና እንዲሁም በወቅቱ የአገራችንን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በሚመለከት መከተል የነበረባቸውን አካሄድ ለማመልከት የተቀየሰ መስመር ነበር። አቋማችን በተለይ በስር- ነቀሉ የመሬት አዋጅ ምክንያት የወ ቅቱ አቢይ ትግልና ትንቅንቅ፤ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ጭቁን ገበሬዎችና በሌላ በኩል ደግሞ በቀድሞ ገዢ መደቦችና ባለመሬቶች መካከል ስለነበረ፤ በዚህ አሰላለፍ ውስጥ ደርጉ፣ ምንም እንኳን የወላዋይነትና የፀረ ዴሞክራቲክ ባህሪዎች ቢያንጸባርቅም፤ በተጨባጭ በነበረውም ሁኔታ፤ ይህ አቋም ድርጅ

ታችን በፍፁም ተቃውሞ አካሄድ የመሬቱን አዋጅ ከሚቃወሙ ፊውዳሊ ስቶችና ፀረ-ኢትዮጵያ ባዕዳን ጎን ተሰልፎ ደርግን ያለመዋጋት ይዘት ቢኖረውም ለአብዮቱ መግፋትና ለስር-ነቀሉ የመሬት አዋጅ እውንነት ሲባል ደግሞ የደርግን አካሄዶች ከመቃወምና ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊቶቹን እያ ወገዘ በሕዝባዊ ጥያቄዎች ዙሪያ ሕዝቡን ከመቀስቀስና ትግሉን ከማራመድ አላገደውም ነበር።

በዚህ ሁኔታ የመሬቱን አዋጅ በተከተሉት ወራት የአገራችን ገበሬዎች ነቅተው፣ ተደራጅተውና ታጥቀው አብዮቱን ከቅልበሳ እንዲከላከሉ፣ በአገኙት መብት ተጠቅመው በያሉበት ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እንዲበቁ „የገበሬ ማህበራት ማጠናከሪያ አዋጅ" እንዲወጣ፣ የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመፃፍ የመሰብሰብ መብቶች እውን እንዲሆኑ፣ በዴሞክራቶችና በአገር ወዳድ ሃይሎች ላይ የሚካሄዱ የአፈናና የወከባ እርምጃዎች እንዲቆሙ ... ወዘተ እያለ ደርጉ በአብዮቱ ሂደት ላይ የሚጋርጣቸውን እንቅፋቶች እያጋለጠና እየተቃወመ፣ ከሌሎች ተራማጅ ሃይሎች፣ ከአገራችን ሠራተኞችና ገበሬዎች ጎን ተሰልፎ ያላሰለሰ ትግል አካሂዷል። ከዚህ አንፃር ሲታይ መኢሶን፣ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፣ ከደርግ ጎን የተሰለፈ ድርጅት ተደርጎ የሚቀርበውን የአሉባልታ አነጋገር ወደጎን ትተን፣ ድርጅታችን ሂሳዊ ድጋፍ አቋሙን በሥራ ላይ ያዋለው በሁለት ወቅቶችና በሁለት የተለያዩ ደረጃዎች ነበር።

የመጀመሪያው ወቅት ከየካቲት 1967 ዓ. ም. እስከ ሚያዚያ 1968 ዓ. ም. የነበረው ወቅት ነበር። በዚህ ወቅት መኢሶን ከደርግ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ትብብር ሳይመሰርት፣ በተለይ የገጠርን መሬት አዋጅ በሥራ ለመተርጎም በሚደረገው ትግል በሙሉ ሃይል ተሳትፏል። ለዚህም በርካታ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን በመሬት ይዞታ አስተዳደር ሚኒስቴርና በእድገት በህብረት፣ የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ጣቢያዎች በማሰማራት ታግሏል። እዚያው በዚያው ደግሞ፣ በወቅቱ፣ ከፍ ብለን በጠቆምነው መልክ ተጨባጭ ዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ጥያቄዎችን አንግቦ የደርግን ፀረ ዴሞክራቲክ አካሄድ እያወገዘና እየተዋጋ ለአብዮታዊ እርምጃዎች ድጋፍ፣ ለአብዮቱ መግፋትና ከቅልበሳ መትረፍ ሲባል ደግሞ ሂስ የሚያቀርብበት ወቅት ነበር።

ሁለተኛው ወቅት፣ ከሚያዝያ 1968 ዓ. ም. እስከ ነሃሴ 1969 ዓ. ም. የነበረው የአስራ አምስት ወራት ጊዜ ነበር። ይህ አዲስ ምእራፍ ሊከፈት የቻለው ከመ ሬቱ አዋጅ አንስቶ መኢሶንና ሌሎች የአገራችን ተራማጆች በመጀመሪያው የትብብር ወቅት ሲያነሷቸው ለነበሩት ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎች አወንታዊ ምላሽ በመስጠት የሚያዝያ 13 1968 ዓ. ም. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በመታወጁ ነበር።

በመኢሶን አቅራቢነት የፀደቀው ይህ ፕሮግራም ከመውጣቱ ቀደም ብሎ ከደ ርግ መሪዎች ጋር፣ ከጥቅምት 1968 ዓ. ም. ጀምሮ ይካሄዱ በነበሩት ድርድ

ሮች አማካኝነት ድርጅታችን በመሬት ይዞታ ሚኒስቴር ረቅቆ፣ የደርግን ይሁንታ ያላገኘው፣ የገበሬ ማህበራትን ማጠናከሪያ አዋጅ ዕውን እንዲሆን፣ የታሰሩ ተራማጆች በሙሉ እንዲፈቱ፣ ዘመቻውን ላቋረጡ ተማሪዎች ምህረት እንዲደረግ የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበው ታህሳስ 1968 ዓ. ም. የደርግ መሪዎች ሃሳቡን በመቀበላቸው ለቀጣይ ትብብር በር ሊከፍት ችሎ ነበር።

ድርጅታችን „ሁለተኛውን የገጠር አብዮት አበሰረ" ያለው የገበሬ ማህበራት ማጠናከሪያ አዋጅ በወጣበት ታህሳስ 14 1968 ዓ. ም ለሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅ/ቤት የተመረጡ 14 ዜጎች ገና ይፋ ባልሆነ መንገድ ተሰይመው ሥራቸውን ከጀመሩ ወር በማይሞላ ጊዜ፣ ጥር 8 1968 ዓ. ም "ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በሥራ ለማዋል" የሚል አዋጅ ረቂቅ አቅርበው በደርግ ጠቅላላ ስብሰባ ተቀባይነት ያገኛል። ይህ ከዛሬ ነገ ይታወጃል እየተባለ ሲጠበቅ፣ በተከሰተው ቅልበሳ ምክንያት ጨርሶ ሳይታወጅ የቀረ ረቂቅ በዴሞክራሲያዊ መብቶች ጉዳይ ከየካቲት ማለዳ ጀምሮ ተራማጆች ያቀርቧቸው ለነበሩት ጥያቄዎች አወንታዊ መልስ የሚሰጥ አዋጅ ነበር።

በመደራጀት መብት ጉዳይ ደርግ ቀደም ሲል ያራምድ የነበረውን የአንድ "መደበኛ የወዝአደሮችና የአርሶ አደሮች ፓርቲ" የሚለውን አካሄድ ሽሮ "ትርጓሜ" በሚለው ክፍሉ "ፓርቲ ማለት የአንድን መደብ ጥቅም መሰረት በማድረግ የተዘረዘረ የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ በመመርኮዝ መንግሥታዊ ስልጣን ለመያዝ የሚታገል ድርጅት ነው።" ካለ በኋላ በአንቀፅ 11 ላይ "ማንኛውም ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ካፒታሊስት የሆነ የሕዝብ ወገን የፖለቲካ ፓርቲ የመመስረት መብት" እንዳለው የሚያረጋግጥ ነበር።

ሆኖም በዚህ መልክ ለማንኛውም ጸረ ፊውዳል፣ ጸረ ኢምፔሪየሊስትና ጸረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎች የመደራጀት መብት መታወቁ በሃገራችን ለመድበለ ፓርቲ ስርዓት መንገዱ ተከፈተ ማለት አልነበረም። በወቅቱ በተራማጆች ሰፈር ሰፍኖ የነበረው የማርክሲስት ርዕዩተ ዓለም ስለነበረ ይህ ከሰራተኛውና ከገበሬው ውጭ ላሉ መደቦችና ሃይሎች የታወቀው የመደራጀት መብት እዛው በዛው ደግሞ በአንድ በወዝ አደሩ የሚመራ አብዮታዊ ግንባር እንደሚጠቃለሉ ብቻ ሳይሆን፣ ቀጣዩን ሂደት በተመለከተ ምርጫ ተደርጎ በወዝ አደሩ መሪነት የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ እንደ ሚቋቋም ይገልጽ ነበር። የተባለው ምርጫ „የግንባሩ አባል ድርጅቶችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸው ምልምሎች መሃከል ሕዝቡ በሙሉ ነጻና ምስጢራዊ በሆነ ምርጫ እንደራሴዎቹን ይሰይማል" የተባለበት አካሄድ ነበር። እንዲህ ከሆነ ህዝቡ ከወዝ አደሩ ፓርቲ ውጭ ላሉት ድርጅቶች ምል ምሎች አብላጫ ድምጽ ቢሰጥ በምን ተአምር የኢህዴሪ መንግሥት „በወዝአ ዳሩ ፓርቲ መሪነት„ ይቋቋማል? ፕሮግራሙ ለዚህ ቁልፍ ጥያቄ ወይም ቅራኔ መልስ የለውም።

ይህም ሆኖ ከአብዮቱ ቅልበሳ ጋር ከተከሰተው የአንድ ፓርቲ ቶታሊቴሪያን

የጨለማ አገዛዝ አንጻር ሲታይ እነዚህም ቅራኔዎች እንዳሉ ሆነው፤ ሌሎች ፓርቲዎች ድርጅታዊ ነጻነታቸው ተከብሮላቸው መንቀሳቀስ የሚችሉበት ሁኔታ ቢኖር ኖሮ ይህ ከፊት የማለት አዝማሚያ ለቀጣዩ የሃገራችን የፖለቲካ ሂደት አወንታዊ አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችል ነበር የሚል ዕምነት አለን። የሰደድ መሪዎች ከዚህ አካሄድ የተንሸራተቱበትም ዋና ምክንያት እንዲህ ዓይነቱ ከፊት ማለት በሂደት ስልጣናችንን አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል ከሚል ስሌት እንደሆነ መገመት ይቻላል።

ሚያዚያ 13 1968 ዓ. ም. ታውጆ ለደርግና ለመኢሶን ትብብር መሰረት የሆነው "የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም" በበኩሉ በዚህ ያዋጅ ረቂቅ መንፈስ የመደራጀትና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ተቀብሎ ሕዝቡና ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት ሃይሎች በነዚህ መብቶች ተጠቅመው ትግላቸውን እንዲያ ፋፍሙና አብዮቱን ከግብ እንዲያደርሱ የሚጠራ ሰነድ ነበር።

በኢኮኖሚው ዘርፍ ብንሄድ "ብሄራዊ ዴሞኪራሲያዊ አብዮታችን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት እንጅ ፀረ ካፒታሊስት አይደለም" የሚለውን የወቅቱን የተራማጅ ሃይሎች አቋም በመከተል፤ የኢኮኖሚውን ዘርፍ የሚያራምዱት ነጋዴዎች፣ ባለኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ብሄ ራዊ ባለንብረቶች አገራቸውንም፣ ራሳቸውንም ለመጥቀም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የመንግሥት ድጋፍ እንደሚያገኙ ቃል ይገባል። በብሄሮች መብት ጉዳይ፤ ብሄሮች የእራሳቸውን ዕድል በእራሳቸው የመወሰን መብት እንዳላቸውና በሪጅናል ኦቶኖሚ መርህ መሰረት በሥራ ላይ እንደሚውል፣ በአገሪቱ ብሄራዊ ነፃነት ጉዳይ ደግሞ ኢትዮጵያ፣ በወቅቱ ዓለምን ሲያናውጥ ከነበረው ቀዝቃዛ ጦርነት ወገናዊ የሆነ አቋም ሳትወስድ በፍፁም ገለልተኛነት፤ ብሄራዊ ጥቅምንና ነፃነትን በሚያስቀድም የውጭ ፖሊሲ እንደምትመራ፤

የግብርናን ፖሊሲ በተመለከተ፣ አርሶ አደሮችን በማገዝና በማበረታታት ላይ የተመሰረተ አካሄድ እንዲሰፍን ... ወዘተ የሚያቀድ ፕሮግራም ነበር። ሆኖም፣ ከጥር 26 1969 ዓ. ም. ኮሎኔል መንግስቱ የእነአለማየሁ ሃይሌን ቡድን አስወግደው ስልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ፤ በአብዮታዊ ሰደድ ቁጥጥር ስር እየወደቀ የሄደው ደርግ የረቀቀውን የዴሞክራሲያዊ መብቶች አዋጅ ይፋ ማድረግ ቀርቶ በግልጽ ከተቀበለው የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮ ትፕሮግራም እየተንሸራተተ፤ አርሶ አደሩ በትግሉና በመስዋዕትነቱ የተጎናጸፏቸውን የፖለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ መብቶች መልሶ ከመቀማት ጀምሮ በሠራተኛው፣ በምሁሩ፣ በወጣቱና በጠቅላላው ለዴሞክራሲ በቆመው ሃይሎች ላይ አፈናና ሺብርን አሰፈነ።

ከዚህ የመንሸራተት ሂደት ጋር መኢሶን ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ ይገባል። በተያያዘም ኢህአፓ፣ መስከረም 16 1969 ዓ. ም በመርካቶ፣ ምንም ትጥቅ

ባልነበራቸው፣ የጥናት ክበብ ተሳታፊዎች በነበሩ ወጣቶች ላይ ተኩስ ከፍቶ ስድስቱን በመግደሉ፣ ቀጥሎም፣ ፍቅሬ መርድንና የመኢሶን "ወጣት ንቅናቄ" ሰብሳቢ የነበረውን ገብረ እግዚአብሔር ሃጎስን፣ በተከተሉት ወራትም ያልታጠቁ ወጣት መሪዎችንና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ታጋዮችን በመግደል የከፈተውን ነጭ ሽብር በአገሪቷ አራቱም ማዕዘናት ያስፋፋል።

„በዚህ በጦር ሰፈሮች፤ በታጠቁ የመንግስት ሃይሎች ላይ ሳይሆን ምንም ትጥቅ በሌላቸው ወጣቶች፤ የሕዝብ ተመራጮች ላይ ያተኮረ የነጭ ሽብር ዘመቻን ለመቋቋም መኢሶን የተሰማራው የሕዝቡ የትጥቅና የዴሞክራሲ ጥያቄዎች መልስ አግኝተው አብዮቱ ከቅልበሳ እንዲድን ያላሰለሰ ቅስቀሳ በማካሄድ ተግባር ነበር። በዚህም መሰረት በወቅቱ በሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎችም ሆነ ሕዝባዊ ስብሰባዎች „አስታጥቁን አታስጨርሱን" „ልምጫችን አስጠቃችን" „ወይ አስታጥቁን ወይ ትጥቅ አስፈቷቸው" የሚሉት መፈክሮች በተደጋጋሚ የሚነሱ ነበሩ።"

እየጎሉ ከመጡት ልዩነቶች መካከል፤ የጀመሪያው በዴሞክራሲያዊ መብቶች መታወጅ ወይም አለመታወጅ ጥያቄ ላይ የተከሰተ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅታችን በብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ በታለመው መሠረት፤ የገለልተኛነት ፖሊሲ ሲያራምድ የሰደድ አመራር ግን "ዓለም አቀፋዊነት" በማለት ከሶቪየት ተስፋፊዎች ጋር የመሠረተውን ግንኙነት የሚመለከቱ ነበሩ። ይህን በተመለከተ፤ ድርጅታችን በሚያወጣቸው አቋም መግለጫ ጽሁፎች ላይ በራስ ስለመተማመንና በብሄራዊ ነፃነት ጉዳይ የሶቪየቶችን አካሄድ እየተቸ፤ ሁኔታው "ለአብዮታችን ብቻ ሳይሆን፣ "ለዘለዓም በነፃነት ትኑር" ለምንላት አገራችን ብሄራዊ ነፃነት አደገኛ እንደሆነ ለማስረዳት ሞከረ። ከመጋቢተ 1969 ዓ. ም. ጀምሮ በሚገደሉ አባሎቻችን ቀብር ስነ ሥርዓት ላይም ሆነ በሌላ አጋጣሚ በሚደረጉ ሰልፎች ሁሉ "ብሄራዊ ነፃነት" የሚለው መፈክር በሰፊው እንዲስተጋባ ጣረ። ይህ አካሄድ "አገራችንን አጋዥ አልባ ለማድረግና አብዮቱን ለመቀልበስ የተጠነሰሰ ሴራ" ብለው ከተረጎሙት የሰደድ መሪዎች ጋር ከፍተኛ ቅራኔ ውስጥ ያስገባዋል።

ስለሆነም፣ ከደርግ ጋር ለተፈጠረው ትብብር መሰረት የነበረው የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮገራም ተግባራዊነት እየተሻረ በመሄዱ፤ መጋቢት1969 ዓ ም. አጋማሽ ላይ፣ ከየአካባቢው የመጡ ተወካዮች በተገኙበት፣ በህቡዕ ባካሄደው ሰፊ ብሄራዊ ኮንፈረንስ የትግል ስልት ለውጥ ለማድረግና ከደርግ በይፋ ተነጥሎ ወደ ህቡዕ ትግል የሚዞርበት ሁኔታ እንዲመቻች ወስኖ አንድ ኮሚቴ መረጠ።

በቀጠሉት ወራት በኢሕአፓ መከፋፈልና መዳከም እንዲሁም በተወሰኑ ቀበሌዎች መታጠቅ ሳቢያ፤ የነጭ ሽብሩ ዘመቻ ጋብ ቢልም፤ አሁን ደግሞ ከሰደድ መሪዎች ጋር ቅራኔዎቹ እየሰፉ ከመሄድ ጋር በድርጅታችን አባላትና መሪዎች ላይ፣ በወቅቱ "ቀለም የለሽ" ያልነው የሽብርና የግድያ ዘመቻ ይጀመ

ራል። ይህ እንደ አለፉት ወራት "በቅጥር ነፍሰ ገዳዮች" ሳይሆን "በአልታወቁ ሰዎች" እያልን ማውገዝ የጀመርነው የሽብርና ግድያ ዘመቻ ከሰኔ 1969 ዓ. ም. ጀምሮ እየተስፋፋ መጥቶ፤ እነአብዱላሂ ዩሱፍ፣ አንበርብር በላይ፣ ዶ/ር መኮንን ጆቴ፣ ተስፋየ ታደሰ፣ ግዛው ጂማ... የመሳሰሉትን መሪዎቻችንና ሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ጓዶችና ጓዲቶች ያጣንበት ጥቃት ይሆናል።

ከሶማሌ ወረራ ጋር በተያያዘ ደግሞ፤ ይህንን ወረራ ምክንያት በማድረግ፣ በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ፣ ሃረርጌ ሲዳሞ፣ ባሌ ... ወዘተ በወታደራዊው ቢሮክራሲና በየክፍለ አገሩ በሚገኙ የደርግ ተወካዮች ትእዛዝ በመቶ የሚቆጠሩ መሪዎቻችንና አባላት "ጠባብ ብሄረተኛ፣ የሶማሌ ሰርጎ ገብ" እየተባሉ ተረሸኑ። በዚህ መልክ፣ ስር እየሰደደ የመጣውን የአብዮት ቅልበሳና የሽብር ሂደት በተሻሻለ ሁኔታ ለመቋቋም፤ መኢሶን በነሃሴ ወር 1969 ዓ. ም. ከደርግ ጋር መስርቶት የነበረውን ትብብር አቋርጦ በህቡዕ ለመታገል ተነሳ። በቀጠሉት አመታት፣ መቀልበስ ያቃተን የቅልበሳ ሂደት ቀጥሎ እንደዚያ ደምቆ ያበራው የየካቲት አብዮት የዴሞክራሲና የነፃነት ችቦ፤ የኢትዮጵያ ልጆች ባፈሰሱት ደም ባህር ሰምጦ ከሰመ። በአብዮታዊ ትግል ተገኝተው የነበሩት ድሎች ተራ በተራ ተነጠቁ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ድሎች ላለመነጠቅ ያካሄዳቸውን ትግሎች ለመደምሰስ ከ1970 ዓ. ም ጀምሮ ደርግ በተሰማራባቸው የቀይ ሽብርና የአረመኔያዊ፣ የጅምላ ጭፍጨፋ አገራችን በታሪኳ አይታም ሰምታም በማታውቀው ዙሪያ ገጠም የቀውሶች አዙሪት ውስጥ ወደቀች።

ቅልበሳው እየገፋ ሄዶ፣ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የተ ለመው "የብዙ ፓርቲዎች መርህ" ተሽሮ አንድ ፈላጭ ቆራጩ ፓርቲ አገሪቱን ተቆጣጠረ። ፕሮግራማችን የቆመለት የገለልተኛነት ፖሊሲ ድባቅ ተመትቶ አገራችን የሶቪየት ተስፋፊዎች ሰለባ ሆና ብሄራዊ ነፃነቷ ተገፈፈ። የብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ያጸደቀው የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትና ዴሞክራሲያዊ የሆኑ የአካባቢ ራስ አስተዳደር ሃሳብ ቀርቶ የመላ አገራችን ብሄሮች በአንድ አምባገነን ድርጅት ስር፤ ለፍፁም አሃዳዊ፣ ፀረ ሕዝብ አስተዳደር ተዳረጉ።

ቀደም ብሎ በታወጀው የገበሬ ማህበራት ማጠናከሪያ አዋጅ ተጠቅመው በያለ በት ምርታቸውንና መብታቸውን እጃቸው አስገብተው አዲስ ኑሮ መገንባት ጀምረው የነበሩት የአገራችን ገበሬዎች መሬታቸውን ታቅፈው፤ ምርታቸውን በኮታ ስም የሚነጠቁበት፣ በዴሞክራሲያዊ ዘዴ መርጠው "የኛ" የሚሏቸው ማህበራት ፈራርሰው፣ መሪዎቻቸው ታስረውና ተሰድደው፤ በሰደድ ካድሬዎች "አመራር" ስር የወደቁበት ሁኔታ ተፈጠረ።

ፕሮግራማችን በኢኮኖሚ መስክ የአገራችንን ነጋዴዎችና ባለሃብቶች በሚያግዝና በሚያበረታታ ፖሊሲ ጭምር ጠንካራ ብሄራዊ ኢኮኖሚ የመገን ባቱ ጉዳይ ተሰርዞ አገራችን "በሶሻሊዝም ግንባታ" ስም የእዝ ኢኮኖሚ ተተ

ክሎባት፤ በህብረት እርሻ፣ በመንደር ምስረታ፣ ወዘተ፣ የጥፋት ፖሊሲዎች እየደቀቀችና እየተዝረከረከች ሄደች። አገራችን ከዚህ የድል ንጥቂያ ጋር ተያይዘው ከተከሰቱት ቀይ ሽብር፣ የክፍለ ዘመኑ ረሃብ፤ ሕዝባችን በሚሊዮን እየተቆጠረ ለስደት፣ ለእንግልት፣ ለማያባሩ ጦርነቶች፣ ለአፈና፣ ለእስራት... ወዘተ በአጭሩ ከፀሀይ በታች አለ የሚባሉ መቅሰፍቶች ተጋግዘው የሚጨፍሩባት ህልውናዋ ሳይቀር ከባድ ፈተና ላይ የሚወድቅበት የዙሪያ ገጠም ቀውስ ውስጥ ገባች።

መኢሶን እንደ ድርጅት፣ መጀመሪያ ከመስከረም 69 እስከ ጥር 69 ነጭ ሽብር፤ ከዚያም ከሰኔ እስከ ጥቅምት 1970 ቀለም የለሽ የግድያ ዘመቻ፤ ከዚያም ቀጥሎ ደግሞ ቀይ ሽብር እየተባለ በተፈራረቁ አመጾች ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት የከፈለ ድርጅት ነው።

ሆኖም ለኢትዮጵያ አብዮት ድሎች፣ ከሕዝብ ጎን ተሰልፎ፣ በከፈለው መስዋዕትነትና ባደረገው አስተዋፅዖ የሚኮራውን ያህል፣ በዚያ ሂደት ውስጥ፣ የፈፀማቸው ስህተቶችና የተንጸባረቁት ድክመቶች ለቅልበሳው መቀጠልና ለዚህ ለተከሰተው ቀውስ አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ይቀበላል።

ሂሳዊ ድጋፍ የሚለው አካሄድ በወቅቱ ከነበሩት ቅራኔዎች አቀማመጥና የሃይሎች አሰላለፍ አንፃር፤ በየካቲት አብዮት የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጎናጽፏቸው ለነበሩ፤ በተለይ በገጠር ለተደረገው ትግል የጠየቀውን መስዋዕትነት ተከፍሎበት ቢሆንም፤ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረገ ትክክለኛ አቋም ነበር። ቢሆንም፣ በነበሩት ተጨባጭ ሁኔታዎች ይህንን መስመር በተግባር መተርጎም እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ እንደነበረ አይካድም። በተግባር አፈፃፀም ላይ ድርጅታችን የፈፀማቸው ስህተቶች በእራሱ በመኢሶን ታጋዮች፣ አንድ ትውልድ ላይ ለደረሰው ጥቃትም፣ ከዚያም አልፎ ለአብዮቱ መቀልበስ ተጠያቂነት፣ አስተዋፅዖ ያደረጉ መሆናቸው የሚካድ አይደለም።

ከነዚህ ድክመቶች እንደ ዋና ዋና ከሚቆጠሩት መካከል የመጀመሪያው በሂሳዊ ድጋፍ መስመር ከደርግ ጋር በተሰማራበት ወቅት በርካታ አባላቱንና ዋና ዋና መሪዎቹን በይፋና በህጋዊ ትግል ማሰማራቱ ነበር። ይህ ደግሞ የሴኩሪቲ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ለህቡዕ ሥራው የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል ያሚጠጠ፣ የድርጅቱን ገመና ያጋለጠ፣ ነፃ ህልውናውን አደጋ ላይ የጣለ፣ በይፋ ትግሉና በእለት ከእለት ተግባራት ተወጥሮ የትግሉን ጉዞ ቆም ብሎ የማየት፣ ለቀጣዩ ትግል የሚያገለግሉ የማፈግፈጊያና የመከላከያ አምባዎች፣ በተመረጡ አካባቢዎች እንዲመቻቹ አስፈላጊው ትኩረት ሳይሰጣቸው እንዲቀር አድርጓል።

ሁለተኛው ትልቅ ግድፈት፣ ገና ሲፈጠር ጀምሮ "የተራዘመ ትጥቅ ትግል" አስፈላጊነትን ቢቀበልም፤ አልፎ ተርፎም በአብዮቱ ወቅት" ለነቃ፣ ለተደራጀና ለታጠቀ ሕዝብ ትግል" በሚል መፈክር ስር ቢንቀሳቀስም፤ ለዚህ አይነቱ አካሄድ አስፈላጊ የሆነውን ትኩረት ሰጥቶ በቂ ዝግጅት አለማድረጉ ነበር። በህጋዊ መድረክ የተሠሩት ሥራዎች ሰፊው ሕዝብ ለስልጣን ፍልሚያ ለሚያ

ደርገው ዝግጅት አስፈላጊ ቢሆኑም በራሳቸው ሰፊውን ሕዝብ ለስልጣን የሚያበቁት አልነበሩም። ይህ እንዲሆን በተጠናከረ የህቡዕ ድርጅትና ትጥቅ መቋጠር ነበረበት።

በፖለቲካው መስመር ብንሄድ ሁለት ዋና ዋና ሊባሉ የሚችሉ ስህተቶች ነበሩ። መጀመሪያ በዴሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ዙሪያ ከሰደድ መሪዎች ጋር የተከሰተውን ልዩነት ይመለከታል። ከፍ ብሎ እንደ ተወሳው ደርግና መኢሶን ተባብረው እንዲሰሩ ያበቃቸው፤ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት፣ ድርጅታችን ለዚህ ትብብር እንደቅድመ ሁኔታ ያቀረበውን፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕረፐግራምና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በሥራ ላይ ለማዋል ያቀረበውን የአዋጅ ረቂቅ በመቀበሉ ነበር። ሆኖም በተለይ ከጥር 26 1969 ዓ. ም. በኋላ፤ ምንም እንኳን ኮሎኔል መንግሥቱ ሃይለ ማሪያም ጥር 27 1969 ዓ. ም. ለድጋፍ ሰልፍ በወጣው ሕዝብ ፊት "ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በይፋ እናረጋግጣለን" ብለው ቃል ቢገቡም የዚህ ተግባራዊነት ከዕለት ዕለት የውሃ ሽታ እየሆነ ይሄዳል። በዚህ ሁኔታ መኢሶን ያዋጁን ረቂቅ ይፋ አድርጎ ለሕዝብ ውይይት በመልቀቅ ለሕዝቡ መታገያ ተጨባጭ መፈክር ሊያደርገው ሲችል፤ ይህን ባለማድረጉ ለዴሞክራሲያዊ መብቶች ይደረግ የነበረውን ትግል ተጨባጭነት ነፍጎታል።

የሕዝቡን ወገኖች እያነቁና እያደራጁ መታገል አስፈላጊነት ቢታመንበትም፣ ግንባር ቀደም ነኝ ካለ አይቀር፣ ጥረቱ በአገሪቱ ያሉትን "ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት" ሃይሎችን በቅስቀሳም ሆነ በማደራጀት ጥረቱ ቅድሚያ ለገበሬውና ለወዝ አደሩ ብቻ የሰጠ አሠራር ነበረው። መኢሶን በዚህ በኩል የፈጸመው ስህተት ከእነዚህ ውጭ ላሉ "የአብዮቱ አጋዥ ሃይሎች" ብሎ የሚቀበላቸውን የመንግሥት ሠራተኞች፣ ነጋዴዎች፣ ባለኢንዱስትሪዎችና ብሄራዊ ከበርቴዎች ለማገዝ ጥረት አለ ማድረጉ ብቻ አልነበረም። ከዚህ አልፎ ተርፎ በእነዚህ ወገኖች ላይ ያደርጋቸው የነበሩት ቅስቀሳዎች "አክራሪ የግራ ፖለቲካ" ይዘት ስለነበራቸው ያብዮቱን ሰፈር የከፋፈሉና ያዳከሙ እነደነበሩ የሚካድ አይደለም። መኢሶን በነዚህና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የፈፀማቸውን ስህተቶችና ሌሎች ግድፈቶችን በጥሞና ገምግሞ የደረሰባቸውን ድምዳሜዎች "መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ውስጥ" በሚል ርዕስ በታተመው፣ የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጠር 50፣ እንዳወጣና በተለይ ደግሞ "የመኢሶን ሂሳዊ ግምገማ" በተሰኘ፣ ባለ 68 ገፅ ሰነድ፣ ዘርዘር ባለ መልኩ ቀደም ሲል አቅርቦ እንደነበር ለአንባቢያን መጠቆም እንወዳለን። በዚህም ከላይ በመቅድሙ መጀመሪያ ላይ „ባለፉት አስርተ አመታት ስለጋራ ትግል እንጂ ስለራሱ ምንም ዓይነት ማስተዋወቅ ባለማድረጉ አብዛኛው ወጣት ትውልድ በሚገባ አያውቀውም፤ ጥቂቶች የሚያውቁት ቢኖሩም ባሉባልታና በተጋነኑ አሉታዊ ድርጊቶች ነው።“ በሚል የጠቆምነውን ክፍተት ያጠበዋል ብለን እናምናለን። በዚህም ወደ ፕሮግራማችን ማሻሻል እንሻገራለን።

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

የ90ናዎቹ መጀመሪያ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፍኖ የነበረው ቀዝቃዛው ጦርነት እየረገበ የሄደበትና፣ በሶቪየት ህብረት መፈረካከስ የተጠናቀቀበት ሲሆን፤ ኢትዮጵያን በተመለከተ፤ የምእራብ ሃያላንና የአካባቢው አድሃሪ አረብ መንግሥታት „በኮሚኒስቱ" ደርግ ላይ በነበራቸው ጥላቻ በመገፋፋት፤ ከጠባብ ብሄረተኛ አማጽያን ጋር አብረው፤ በግንቦት ወር 1983 (1991) ዓ.ም. በስመ ጥፋው የለንደን ኮንፈረንስ አማካይነት የኤርትራን መገንጠልና በቀረው የአገሪቷ ክፍል ላይ ደግሞ፤ በዴሞክራሲያዊ ሽግግር ስም ፈላጭ ቆራጭ፣ የሆነ ከአነድ አናሳ ብሔር የወጣ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የበላይነት አገዛዝ እንዲተከል አደረጉ።

በመሆኑም፣ ጎጠኛው ህወሃት አዲስ አበባን ሲቆጣጠር አገሪቱን „እኔው በመሰለኝ፣ እኔው ወደምፈልገው ሥርዓት አሸጋግራለሁ፤ እኔው ሽግግሩን በሞግዚትነት እመራለሁ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ፖሊሲዎች እኔው ባሻኝ እቀይሳለሁ" ከሚሉት፣ ወቅታዊ ከሚመስሉ ጥያቄዎች አልፎ የአገራችንንም ህልውናና አንድነት በሚመለከተው በኤሪትራም መገንጠል ጉዳይ „ያሻኝን አቋም አራምዳለሁ" የሚል ሃይል አገራችንን ተቆጣጠረ። ከዚያ ወዲህ የሆነውን ሁላችንም እናውቀዋለን።

የኤርትራ ሕዝብ „ከባርነት ወይም ከነፃነት" የሚል ሸውራራ አማራጭ ቀር ቦለት ከእናት አገሩ ከኢትዮጵያ ተገነጠለ። አገራችን ወደብ አልባነት ተፈረደባት። በዓለም ላይ ተደርጎ የማያውቅ፣ በዘር ላይ የተመሰረቱ የፖለቲካ ቡድኖች እንደአሸን እንዲፈሉ ተደረገ። የዘር ግጭቶች እንዲፋፋሙ ሆነ። „በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ" ስም በወያኔ/ኢህአዴግ ዙሪያ የተኮለኮሉ ጥቂቶችን ለናጠጠ ሀብታምነት፣ ብዙሀኑን ደግሞ ከዕለት ዕለት እየከፋና እየሰፋ ለሚሄድ ማጣትና መራቆት የዳረገ ሙሰኛ „የስድ ገበያ ኢኮኖሚ" ተተከለ። በብ ሄሮችም እኩልነት ስም „አንድ ብሄር እወክላለሁ „እያሉ የሚቀጥፉ የትግራይ ሕዝብ ነጻነት ግንባር በሚል የተሰባሰቡ ሃይሎችና እንደ እነሱው „ብሄራችንን እንወክላለን" በሚሉ ሌሎች ጥቂት ቀጣፊዎች ትብብር „በዴሞክራሲያዊ ፌዴሬሺን" ስም በጥቂት አምባገነኖች ቁጥጥር ስር የሚሠራ፤ የብሄሮችን በየአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ዴሞክራሲያዊ መብት የገፈፈ፣ የብሄሮችን በጋራ የአገር ጉዳይ ተመጣጣኝ ተሳትፎ መርህ ገደል ያገባ፣ በህወሃት ጥቂቶች ቁጥጥር ስር የወደቀ ፍጹም ጨቋን አገዛዝ ተደነገገ።

የየካቲትን መሬት ላራሹ አዋጅ ቀልብሶ፤ መሬት የአራሹ ሳይሆን የመንግ ሥት አድርጎ፤ ያገራችንን ገበሬዎች ለመንደር ካድሬዎች ጢሰኝነት የዳረገ፤ በዚህም ሳቢያ የርሃብና የሰቆቃ አዙሪት እንዲቀጥል የሚያደርግ ሥርዓት ተደ

ላደለ ... ወዘተ። ይህንን ሁሉ ለመቆጣጠር ዛሬ ድፍን ዓለም የተቀበላቸውን

ሞክራሲያዊና የመልካም አስተዳደር እሴቶች ሙሉ በሙሉ የሚፃረር፣ ያለፈው ክፍለ ዘመን፣ ያረጀና ያፈጀ፣ ስታሊናዊ ህገመንግሥት ተደነገገ።

ሀገሪቱን በጎሳ በመከፋፈል ክልል በሚል የጎሳ ፌዴራሊዝምን ፈጥሮ ለከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካው፤ አንዱን ጎሳ ከሌላው ጋር በማጋጨት፤ አንዱን ሃይማኖት በሌላው ላይ በማነሳሳት፤ አንዱ ሌላውን የጎሪጥና በጥርጣሬ እንዲያይ በማድረግ በሕዝብ መካከል ዳብሮ የቆየን የፍቅርና የመተባበር አብሮነት በማላላት፤ ሕብረተ-ሰቡን አመሰቃቅሎታል። የሀገሪቱን የእርሻ መሬቶች ለውጭ ባለሃብቶች እስ99 አመት በሚቆይ ውል እዚህ ግባ በማይባል የኪራይ ሒሳብ ለማከራየት፤ ባስር ሺህ የሚቆጠሩ ገበሬዎችን ያለፈቃዳቸው በግዳች ያለምንም በቂ ዝግጅት ከቀያቸው በማፈናቀል ለረሃብና ለተለያዩ ችግር ዳርጓል። አንዱ ጎሳ ወደሌላው ክልል እንደልቡ ተዘዋውሮና ሰርቶ የፈለገበት ቦታ እንዳ ይኖር በማድረግ፤ ለዘመናት ከኖረበት ቦታ በመጤነት እንዲባረር በማድረግ ሕዝብን ከሕዝብ ጋር በማቃረን፤ የጎሳ ችግሮችን ሆን ብሎ በመቀስቀስ ሕዝብን አጋጭቶ፤ እዚያው በዚያው ደግሞ አስታራቂና ገላጋይ በመምሰል „የሌባ ዓይነ-ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ እንዲሉ“ ያለሱ ጠባቂና አዳኝ እንደሌለ አድርጎ ለማቅረብ በመሻት ባታላይነት ስልጣኑን በማራዛም ይገኛል።

በፌዴራል አስተዳደር አገራቸውን የሚመሩ አገራት እንደየሃገራቸው ተጨባጭ ሁኔታ፤ ለኤኮኖሚ የጋራ ዕድገት፤ አገልግሎቶችን በተለይም የመንግሥት አገልግሎቶችን በቅርብ የማግኘትን አመችነት ባገናዘበ፤ የዜጎችን መራራቅ ሳይሆን፤ መቀራረብን ማዕከል ባደረገና የተለያዩ ሌሎች መስፈርቶችን ጭምር ባካተተ፤ ሕዝብ መክሮበት  ማዋቀር ሲገባ፤ ቋንቋን ብቻ መለኪያ በማድረግ በማንአለብኝነት የፈጠረው ፌዴራሊዝም ለዝንተ ዓለም ተቀላቅሎና ተስማምቶ የኖረን ሕዝብ በማለያየት፤ በመሬት ይገባኛልና በጥቅም ግጭት በየአካባቢው በሚነሱ ግጭቶች የብዙ ሰው ሕይወት አልፏል በማለፍ ላይም ይገኛል። ለወደፊትም ማለቂያ አይኖአረውም።

በአንድ አገር ውስጥ ጠንካራ ኢኮኖሚ የገነቡና የተሻለ ገቢ ያላቸው አካባ ቢዎች፤ እድገታቸው አዝጋሚ ለሆነና ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው አካባቢዎች በሕግ የተወሰነ ድጋፍ የሚያደርጉበት ሕገመንግሥታዊ ድንጋጌ ያላቸው አገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ፤ በሀገራችንም ይሕንኑ መርሕ በመጠቀም አንዱ ክፍለሃገር ሌላውን እንዲደግፍ ማድረግ ሲገባ፤ የጎሳ ክልል በፈጠረው አድላዊነት የሚደረገው የዘፈቀደ የበጀት ድልድልም ሆነ፤ የእድገት እን ቅስቃሴ ለሌለ ቅራኔ መፈጠሪያ መሆኑ ይታያል።

ድርጅታችን ከላይ የተዘረዘሩትን በወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች፣ በሀገሪቱና በሕ ዝቧ ላይ የተደቀኑትን  አደጋ መገንዘብ ብቻ ሳይሆን፤ ችግሮቹ በጊዜው እር

ማት እንዲደረግባቸው ባለፉት ሃያ አንድ አመታት፣ ሌሎች የዴሞክራሲያዊ ሃይሎችንና አገር ወዳድ ዴሞክራቶችን በማሰባሰብ ሲታገል ቆይቷል። በዚህም

መሰረት የፓሪስ አንድን፣ የአዲስ አበባውን፣ የሰላምና የእርቅ ጉባዔን ከዚያ የፈለቀውን „የአማራጭ ሃይሎች ምክር ቤት" ከዚያም የተከተለውን የፓሪስ ሁለት ጉባዔና „የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት (ኢተፖድህ)" እውን ለማድረግ ከአዉሮፓ ወዳጅ ዘመዶች የገንዘብ እርዳታ በማ ሰባሰብና ለትግሉ የፖለቲካ ድጋፍ በማስገኘት፣ በሃሳብም ደረጃ ለነዚህ ጉባዔዎችና ከነሱ ለፈለቁ ስብስቦች፣ ወቅታዊ የሆኑ ሰነዶችን በማ ዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ የተጫወተውን ሚና በነዚያ ስብስቦች ተሳታፊ የነበሩ ሁሉ የሚመሰክሩት ነው። በ1997 ዓ.ም. ተደ ርጎ በነበረው ታሪካዊ አገር አቀፍ ምርጫ ተካፋይ የነበረው ሕብረትም ሲቋቋም ድርጅታችን ተመሳሳይ ተሳትፎ ያደረገ ቢሆንም እንኳን፤ ወያኔ/ኢህአዴግ ተልካሻ ምክንያቶችን በመፍጠር የሕብረቱ አባል የነበሩትንና በውጭ የሚገኙትን ድርጅቶች ወደሀገር እንዳይገቡ ቢያደርጋቸውም፤ በሀገር ቤት የነበሩት የህብረቱ አባል ድርጅቶች በምርጫው ተሳትፈው ከቅንጅት ቀጥሎ ሰፊ ድምጽ አግኝተው ተመርጠው እንደነበር ይታወሳል። ይህንን በሃገራችን ሰላማዊ ሽግግር እንዲኖር ለ16 ዓመት የተደረገውን ጥረትና ትግል ውጤት ወያኔ ኢሕአዴግ ጨፍልቆ በጉልበት ሥልጣኑን ይዞ ቀጥሏል። ጸረ-ዴሞክራቲክ አገዛዙም ከቀን ወደቀን እየከፋ በመሄድ ላይ ይገኛል። የሕዝብም ትግል ቀጥሏል።

ብሎም ከዚህ በላይ ባቀረብናቸው አገዛዙ ዛሬ በሚጠቀምበት የመንግሥታዊ አወቃቀርና የተፈጸመውን የሕብረተሰብ መዘበራረቅ ለማስተካከል፤ የሚያስችል አወቀቀር አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤ ድርጅታችን ላለፉት 22 ዓመታት ይዞት የቆየውን የፖለቲካ ፕሮግራም ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። አባላቱና ደጋፊዎቹም በዚህ ፕሮግራም እየተመሩ ከኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች፤ ጋር ተሰልፈውና ተባብረው ለነጻነት፤ ለፍትህና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ይገፉሉ።

# ክፍል ሁለት

# የፖለቲካ ፕሮግራም

## አንቀጽ አንድ

## አላማ

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የዜጎች መብቶች የተጠበቁበት፣ አንድነቷ በብሔሮቿ እኩልነትና በወንደማማችነት መንፈስ ላይ የተመሰረተና ብሔራዊ ነጻነቷ የተከበረ ኢትዮጵያን መመስረት የሆናል።

## አንቀጽ ሁለት

## መንግሥት

1. የመንግሥት ባህርይ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብር፣ የሀገሪቱን ብሔሮች መብት የሚጠብቅና የኢትዮጵያን ሕዝብ የኢኮ ኖሚና ማሕበራዊ መብቶችና ጥቅሞች የሚንከባከብ ይሆናል።
2. የመንግሥት አደረጃጀትና አወቃቀር
   - ሀ. አደረጃጀት/ቅረጽ ፌዴራላዊ ሪፑበሊክ ይሆናል።
   - ለ. አወቃቀሩ ወደፊት በሕገመንግሥቱ የሚደነገግ ይሆናል።
   - ሐ. የፌዴራሉም ሆነ የፌዴራል አባል መንግሥት በሕግ አውጭ፣ በሕግ አስፈጻሚና በሕግ ተርጓሚ አካላት የተከፈለ ይሆናል።
3. የሕግ አስፈጻሚው አካል በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጥና የሥልጣን ዘመኑም በሕግ የተገደበና ከ2 ጊዜ በላይ የማይወዳደር ፕሬዚዴንታዊ አስተዳደር፣
4. መንግሥት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከሚያቀርቧቸው እጩዎች መካከል ሕዝቡ ተወካዮቹን በነጻ፣ በምስጢራዊና በአጠቃላይ ምርጫ እየመረጠ ይሰየማል።
5. ዳኝነት፣ ከሥራ አስፈጻሚ አካሎች ነፃ በሆነ ሥርዓት ይቋቋማል።
6. ሃይማኖት፣ ከመንግሥት ፈጽሞ የተለየ ይሆናል። መንግሥት ለማ ንኛውም ሃይማኖት እንዳያዳላ ይደረጋል።

# አንቀጽ ሶስት

## ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. የንግግር፤ የጽሁፍ፤ የጋዜጣ፤ ሃሳብን የመግለጽ፤ የምርምር፤ የመሰብሰብ፤ በፖለቲካና በሙያ ማህበሮች የመደራጀት፤ ነጻነቶችና የሰላማዊ ሰልፍና የሥራ ማቆም መብቶች ተከብረው በሥራ ላይ ይው ላሉ።

2. የፖለቲካ፤ የሕዝባዊና የሙያ ድርጅቶች ነጻና ዲሞክራሲያዊ ህልውና የተረጋገጠ ይሆናል።

3. በምርመራ ስም የሚፈጸም ማናቸውም ዓይነት የአካልና የስነ-ልቦና ማጉላላት (ቶርቸር) የተከለከለ ይሆናል።

4. ማንም ዜጋ በፖለቲካ ዕምነቱ፤ አስተያየቱና አቋሙ ምክንያት አይ ታሰርም። ወይንም፤ ማናቸውም ዓይነት ቅጣት፤ መጉላላትና ተጽእኖ አይደርስበትም።

5. ማንም ሰው በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ያለፍርድ አይታሰርም። ወይንም፤ ማናቸውም ዓይነት ቅጣትና መጉላላትና ተጽእኖ አይደ ርስበትም።

6. የያንዳንዱ ዜጋ የመኖሪያ ቤት ነጻነት አለመደፈር፤ በስልክና በመሳሰሉት መገናኛዎች የመገልገል፤ ከቦታ ቦታ በነጻ የመዘዋወር፤ ከአገር የመውጣትና የመግባት መብቶች የተከበሩ ይሆናሉ።

7. ማንም ሰው የአንድ ሃይማኖት ወይንም ፍልስፍና ተከታይ በመሆኑ ምክንያት፤ ወይንም የየትኛውም ሃይማኖት አማኝና ተከታይ ባለመ ሆኑ ምክንያት፤ ምንም ዓይነት በደልና ተጽእኖ አይፈጸምበትም።

8. በፆታዎች መካከል ልዩነት አይደረግም። በተለይ ሴቶች በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚ፤ በባህልና በማህበራዊ ጉደዮች የሚኖራቸው መብቶች በማንኛውም ረገድ ከወንዶች እኩል ይሆናል።

9. መንግስት፣ ለአገራቸው ነፃነትና ክብር ሲያገለግሉ የአካል ወይም የስነልቦና ጉድለት ደርሱባቸው ሠርተው መኖር የማይችሉ ዜጎችን፣ ምንም አይነት አሳዳጊ የሌላቸው ታዳጊዎችንና ምንም አይነት ጡረታ የሌላቸው አዛውንቶችን እንዲሁም ለጎዳና ተዳዳሪነት የተዳረጉ ዜጎ ችን ይንከባከባል ።

10. ማንኛውም ዜጋ፣ በአገሩ ውስጥ፣ የትም ቦታ የመኖርና የመሥራት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።

11. ማንኛውም ዜጋ፣ ያለፈቃዱ ከሚኖርበት ቦታ እንዲለቅ አይገደድም።

# አንቀጽ አራት

## የብሔሮች መብቶችና ነጻነቶች

1. ብሔሮች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው ለመወሰን መብት የታወቀ ይሆናል።

2. የኢትዮጵያ አንድነት፣ የሃገሪቱ ብሔሮች አብሮ ለመኖር ባላቸው ፈቃደኝነት፣ በእኩልነት እርስ በርስ በመረዳዳት በሚያገኙት ጥቅም፣ ላይ የተመሰረተና የተገነባ ይሆናል።

3. እያንዳንዱ ብሔር የራሱን ታሪክ፣ ባህልና ልምድ ለማስፋፋት፣ በራሱ ቋንቋ ለመጠቀም ሙሉ ነጻነት ይኖረዋል። ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ፣ መንግሥት የተቻለውን ድጋፍ ይሰጣል።

# አንቀጽ አምስት

## በሔራዊ ነፃነት

1. ባገር ውስጥ ጉዳይ የማንንም የውጭ መንግሥት ጣልቃ ገብነት በማስወገድ፣ የአገሪቱ ብሔራዊ ነጻነት የተከበረ ይሆናል።

2. የአገሪቱን የልዕልና መብቶች በመቃረን ከማናቸውም የውጭ መንግሥት ጋር የተደረጉ ውሎች ይፈርሳሉ።

3. ባገሪቱ ምድር የማንም ባእድ ጦር እንዳይሰፍር ወይንም የማንም የባዕድ ጦር ሰፈር እንዳይገነባ ይደረጋል።

# አንቀጽ ስድስት

## ኢኮኖሚ

1 የኢኮኖሚ ፖሊሲው የቅድሚያ ቅድሚያ ግብ፣ አገሪቱን በምግብ እራሷን ማስቻል፣ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በሕዝቧ ጉልበት፣ ሀብትና ዕውቀት፣ መተማመን ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድርግ ይሆናል።

2. መንግሥት፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ በተቀላጠፈ መንገድ እንዲያድግና ለመላው ሕብረተሰብ ጥቅም እንዲውል ለማድረግ፣ የሃገሪቱን የጥቅምና የፍላጎት ቅደም-ተከተል የሚያመለክት አጠቃላይ አመልካች ፕላን ያወጣል። በሕግ የሚወሰኑ ስትራቴጂያዊ የኢኮኖሚ ዘርፎች በመንግሥት አስተዳደር ስር እንዲውሉ ሲደረግ፣ ሌሎች የምርት፣ የአገልግሎት፣ የንግድ፣ የማከፋፈያ፣ … ወዘተ ዘርፎች በሙሉ በግልና በሽርክና ለሚሰሩ ባለንብረቶች ይተዋሉ።

3. መንግሥት ከሌሎች መንግሥታት፣ ዓለም-አቀፍ የፊናንስ ተቋሞችና የግል የፊናንስ ድርጅቶች ጋር የገባቸው የኢኮኖሚና የፊናንስ ውሎች ለአገሪቱ ጠቃሚ ሆነው ከተገኙ ይከበራሉ።

4. ኢኮኖሚው እንዳያድግ፣ እንዳይስፋፋና እንዳይዳብር ማነቆ የሆኑ ቢሮክራሲያዊ ተቋሞችና አሰራራቸው እየተጠና፣ እንዲሻሻሉ፣ እን ዲለወጡ ወይንም እንዲዘጉ ይደረጋል።

5. ብሔራዊ ከበረቴዎች፣ ነገዴዎች፣ ባለሙያዎች፣ ቸርቻሪዎችና ... ወዘተ. በማናቸውም በመረጡት ሕጋዊ የሥራ መስክ - በኢንዱስትሪ፣ በንግድ በግብርና፣ በትራንስፖርት፣ በመድሕን፣ በፊናንስ ... ወዘተ. እንዲሰማሩ ይደረጋል።

6. የውጭ ካፒታል ከመንግሥትና ከኢትዮጵያውያን ካፒታል ጋር እየተቀናጀ፣ ላገርና ለሕዝብ በሚጠቅሙ መስኮች ላይ እንዲውል ይደረጋል።

7. የገጠርን መሬት የመንግሥት ንብረት ያደረገው የየካቲት 25 ቀን 1967 አዋጅ በተስተካከለ መንገድ በሥራ ላይ እንዲወል ይደረጋል።

   ሀ. ያራሹ ገበሬ የይዞታና የምርት በላቤትነት ይዞታውንም ለወራሾቹ ለማስተላለፍ መብቶች በሕግ ይረጋገጣሉ።

   ለ. አራሹ ገበሬ ምርቱን በነጻ ገበያ የመሸጥና የመለወጥ መብቱ የተረጋገጠ ይሆናል።

   ሐ. የመሬ የመሸጥ መለወጥ መብት ወደፊት በሕዝበ ውሳኔ መሰ ረት ይደነገጋል።

   መ. የሰፈራና የመንደር ምስረታ እንቅስቃሴዎች በጥናትና በሕ ዝብ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ የማስተካከልና የእርማት እር ምጃዎች ደረጃ በደረጃ ይወሰዳሉ።

8. ነፍስ ወከፍ አራሾችና ኩባንያዎች የግል ሰፋፊ እርሻዎችን በኮ ንትራት የማቋቋም መብት ይኖራቸዋል።

9. መንግስት፣ ለአርሶ አድሩ ዜጋ የፊናንስ፣ የዕውቀትና የቴክኒክ ድጋ ፎችን የሰጣል።

10. እንዱስትሪዎች በመላ አገሪቱ - በተለይም በገጠር እንዲቋቋሙ ማናቸውም ጥርት ይደረጋል። የሃገረ-ሰብ እደ-ጥበብ እንዲያድግ፣ እንዲስፋፋ፣እንዲደራጅና እንዲበለጽግ ይደረጋል።

11. የውጭ ንግድ በመንግሥት መመሪያ መሰረት ይካሄዳል። ለአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገትና ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም የሚውሉ ሸቀጦች ቅድሚያ ይኖራቸ ዋል።

12. መንግሰት ከቀያቸው እያፈናቀለ መሬታቸውን ለውጭ ባለሃብቶች የተሰጠባቸው አርሶ አደሮች ተመልሰው የሚቋቋሙበት ሁኔታ ይፈ ጠርላቸዋል።

13. ከከርሰ ምድር ያሉ የተፈተሮ ሃበቶች የመንግስት ንበረት ናችው።

# አንቀጽ ሰባት

## ማሕበራዊ ጉዳዮች

1. የኢትዮጵያ ሕዝብ መልካም ባህሎችና ጥሩ ልምዶች እንደተጠበቁና እንደተከበሩ ሆነው እንዲደራጁ ይበረታታሉ።

2. የሥነ-ጽሁፍ፣ የኪነ-ጥበብ፣ የቲያትር፣ የሙዚቃና የስፖርት ሰዎችና ድርጅቶች ሁሉ ለህብረተሰቡ አጠቃላይ የባህል ዕድገት የየበኩላቸውን በተሻለ ለማበርከት እንዲችሉ፣ መንግሥት አስፈላጊ የሆኑትን ድጋፎች ይሰጣል።

3. ትምህርት ለአገር እድገት፣ ለሰፊው ሕዝብ ብልጽግናና ደህንነት እንዲስማማ፣ የነፍስወከፍ፣ የብሔሮችን፣ የእምነቶችንና የጾታዎችን የእኩልነት መብቶች በማወቅና በማክበር እንዲያንጽና የሳይንስንና የቴክኔዎሎጂን መስፋፋት መዳበር እንዲያረጋግጥ ሆኖ ይደራጃል።

4. መማር የእያንዳንዱ ዜጋ መብት እንደ መሆኑ መጠን፣ የመንግ ሥት ትምህርት ቤቶች ከማናቸውም ዓይነት ክፍያ ነጻ ይሆናሉ።

5. ትምህርት በየብሔሮች ቋንቋ እንዲሰጥና እንዲስፋፉ ይደረጋል።

6. መሃይምነትን ለማስወገድ፣ የመሰረተ ትምህርት ዘመቻዎች እየተደ ራጁ እንዲካሄዱ ይደረጋሉ።

7. የመንግሥት ሆስፒታሎች፣ ክሊኒኮች፣ የህክምና፣ የማዋለጃ ጣቢ ያዎችና መድሃኒት ቤቶች በየቦታው በብዛት እንዲቋቋሙና እን ዲደራጁ ይደረጋል።

8. ተላላፊ በሽታዎችን ለማጥፋት ተከታታይ ዘመቻ ይደረጋል።

9. ሠራተኞችና አነስተኛ ገቢ ያላቸው ማህበራዊ ክፍሎች ያለባቸውን የመኖሪያቤት ችግር ለመቋቋም፣ መንግሥት የቁጠባ ቤቶችን እየሰራ በዝቅተኛ ዋጋ ያከራያል።

10. ሥራ አጥነትን ለማስወገድና የሥራ ዋስትናን ለማረጋገጥ ማናቸውም ጥረት ይደረጋል።

11. የሳይንስና የቴክኖሎጂ ሰዎችና ድርጅቶች ምርምሮችን በተሟላና በአመቺ አኳሁዋን ለማከናወን እንዲችሉ ማናቸውም መንግሥታዊ እርዳታና ድጋፍ ይሰጣል።

12. ደሞዝተኞች ጡረታ በሚወጡበት ጊዜ የጡረታ አበል ይከፈላቸዋል። የኑሮ ውድነትን በመመርኮዝ የጡረጣ አበል ማደግ የኖረበታል

13. በጦርነት ለተጎዱ የሰረዊትና የሌሎች ጦሮች አባሎችና ሲቭሎች ልዩ የድጎማ አበል ይቆረጣል። በሥራ ለመሰማራት የሚችሉትን መልሶ ለማቋቋም ማናቸውም ጥረት ሲደረግ፤ አካለ ስንኩላን ለሆኑት ልዩ እንክብካቤ ይደረጋል።

# አንቀጽ ስምት

## የሠራተኛ ሕዝብ ጥቅምና መብቶች

1. አንድ ሰራተኛ የሚከፈለው ዝቅተኛ ደመወዝ በሕግ የተወሰነ ይሆናል።

2. አንድ ሰራተኛ በቀን ከስምንት ሰዓት፤ በሳምንት ከአርባ ሳዓት በላይ እንዲ ሰራ አይገደድም።

3. ማንኛውም ሴት ሰራተኛ ከወሊድ በፊትና በሁዋላ፤ በህግ የተወሰነ

   መናቸውም አይነት ክፍያ ወይንም ጥቅም ያልተጓደለ የወሊድ እረፍት የኖራታል።

4. ማንኛውም ሠራተኛ የጤና ኢንሹራንስና የጡረታ መብት ይኖረዋል።

5. ማንኛውም ሰራተኛ ከሙሉ ደሞዙ ጋር የዓመት የዕረፍት ጊዜ ይኖረዋል

6. የሰራተኛ ሴቶችና ቤተሰቦችን ችግር ለማቃለል የማዋለጃ ቤቶችና የህጻናት መዋያ ድርጅቶች እንዲቋቋሙ ይደረጋል።

# አንቀጽ ዘጠኝ

## መከላከያ

1. የአገሪቱ ጦር ሃይል፤ ለሃገሪቱ ሕገ-መንግሥት ታዛዥና ተገዥ ይሆናል።

2. አገሪቱን ከውጭ ጠላቶች ለመከላከል በሚያበቃ ዘመናዊ የጦር ስልትና ትጥቅ የሰለጠነ የመከላከያ ጦር ሃይል እንዲኖር ይደረጋል።

# አንቀጽ አሥር

## የውጭ ጉዳይ

1. የአገሪቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በታወቁት በአምስቱ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆ ላይ ተመስርቶ ይመራል። እነዚሁም፤

ሀ. የአንድን አገር ብሔራዊ ነፃነት፤ ክብርና የግዛት አንድነት ማክበር፥

ለ. በጦርነት አለመፈላለግ፤

ሐ. በሌላው አገር በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፤

መ. በእኩልነትና በጋራ ጥቅም መሰረት መተባበር፤

ሠ. እርስ በርስ መከባበርና በሰላም አብሮ መኖር ናቸው።

2. ከጎረቤት አገሮች ጋር መልካምና ቅርብ የወዳጅነትና የትብብር ግንኙነቶች እንዲገነቡና እንዲደረጁ ማንኛቸውም ጥረት ይደረጋል።

4. የተባበሩት መንግሥታትንና የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ቻርተሮች በመደገፍ፤ ድረጅቶቹ የቆሙላቸው መሰረታዊ አላማዎች በግብር እንዲተረጎሙ ማናቸውንም ጥረት ያደርጋል።

ሚያዝያ 2005 ዓ. ም .